# የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የፕሮግራሞች ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

# ለኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ

# ሚያዝያ 12 ቀን 2002 ዓ.ም

## መግቢያ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከተማ ዘርፍን፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪን እና የመንገድ ልማት ዘርፍን እንዲመራ፣ እንዲያስተባብርና እንዲከታተል የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣትና ክፍለ ኢኮኖሚው ሀገሪቱ የተያያዘችውን የዘላቂ ልማትና ድህነት ቅነሳ ዕቅድን እውን በማድረግ ረገድ የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ለማስቻል በሦስቱም ዘርፎች ሰፊ እንቅስቃሴ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በዚህም መሠረት በልማት ዕቅድ ዘመኑ የቤቶች ልማት ፕሮግራም፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ልማት ፕሮግራም፣ የከተሞች መሠረተ-ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም፣ የከተሞች መልካም አስተዳደር ፕሮግራም እና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አቅም ግንባታ እና የመንገድ ልማት ፕሮግራም አፈፃፀም ሪፖርት እንደሚከተለው በአጭሩ አቀርባለሁ፡፡

## I. የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም

የቤቶች ልማት ፕሮግራም በአዲስ አበባ ከ1999 ዓ.ም. በፊትና በሌሎች ክልሎች ደግሞ ከ1999 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ እየሆነ ያለ ፕሮግራም መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሠረት በፕሮግራም ዘመኑ በትግራይ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ ብ/ብ/ህ፣ በሐረሪ ህዝብ፣ በአዲስ አበባና በድሬደዋ በድምሩ የ171 ሺህ ቤቶች ግንባታ ተከናውኗል፡፡ ከነዚህም ቤቶች በክልሎችና በአዲስ አበባ በድምሩ 72 ሺህ ቤቶች ግንባታቸው ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች ተላልፈዋል፡፡ ፕሮግራሙ የቤት እጥረትን ከማቃለል ባሻገር በከተሞች ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ አነስተኛና መካከለኛ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች እንዲስፋፉ በማድረግ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን አቅም ማጠናከር የሚሉ ዓላማዎችን የያዘ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት እስከ 2002 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ በተለያዩ የሥራ ዓይነቶች በድምሩ 4,306 አነስተኛ የኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዞች ተፈጥረዋል፡፡ በተጨማሪም በቤት ልማት ፕሮግራሙ አማካይነት እስከ 2002 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ በከተሞች 176 ሺህ ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድሎች ለመፍጠር ተችሏል፡፡

ከቤት ልማት ፕሮግራሙ ጋር በማያያዝ ቀድሞ ተደራጅተው ከነበሩት በተጨማሪ በየመሥሪያ ቤቱ ያሉ የምህንድስና ባለሙያዎች በፕሮግራሙ እንዲሳተፉ ዕድሉን በማመቻቸት በሥራ ተቋራጭነትና አማካሪነት አቅም የመገንባት ሥራም ተከናውኗል፡፡ በዚሁ መሠረት በተለያዩ መስኮች በመንግስትና በግል ተቋማት ተቀጥረው በመስራት ላይ ያሉትን የምህንድስና ባለሙያዎችን መስፈርቶችን በማሻሻል የመመዝገብ ሥራ ተሠርቶ በአጠቃላይ 2,353 ባለሙያዎች በፍላጐታቸው የተመዘገቡ ሲሆን ከእነዚህ ባለሙያዎች ውስጥም 752 ያህሉ አዲስ የባለሙያ የሥራ ተቋራጭ ሆነው እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡ እነዚህ የተደራጁት የባለሙያ ሥራ ተቋራጮች ለሥራ ተቋራጭነት የሚያበቃ የስልጠና፣ የፋይናንስና የመሣሪያ ድጋፍ ተደርጐላቸዋል፡፡  በዚህ መልክ ከተደራጁና ከተጠናከሩ በኂላም የሥራ ትስስር ተፈጥሮላቸዋል፡፡ ከእነዚህ የባለሙያ የሥራ ተቋራጮች ውስጥ 584 በቤት ልማት ፕሮግራሙ እየተሳተፉ ሲሆን ቀሪዎቹ 168 የሥራ ተቋራጮች ደግሞ በቴሌ፣ በጤና፣ በዩኒቨርስቲዎችና በመሳሰሉት የመንግሥት የግንባታ ፕሮጀክቶች ውስጥ በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ፡፡  በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በቤት ልማት ፕሮግራሙ ብቻ 1,338 ነባርና 584 አዲስ የባለሙያ የሥራ ተቋራጮች በድምሩ 1,922 የሥራ ተቋራጮች በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህም ቀደም ሲል በቤት ግንባታ ይታይ የነበረው የስራ ተkራጮች እጥረት በከፍተኛ ደረጃ ተቃሏል፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም የተቋራጮቹን የብቃት ደረጃ የማሳደግ ሥራ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በቂ ቁጥር ያላቸውን አማካሪ ድርጅቶችን ለማፍራት በተሰራው ሥራ 147 ባለሙያዎች በ50 አማካሪ ድርጅቶች እንዲደራጁ፣ የሥልጠና እና የፋይናንስ ብድር ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ከእነዚህ አማካሪ ድርጅቶች ውስጥ 43ቱ የሥራ ትስስር የተደረገላቸው ሲሆን ከዚህም ውስጥ 20ዎቹ በቤት ልማት ኘሮግራሙ፣ ቀሪዎቹ 23 ደግሞ በቴሌ ሞባይል ማስፋፊያ፣ በጤና ጣቢያ፣ በቴሌቪዥንና ሬዲዮ ጣቢያና በተንዳሆ ቤቶች ግንባታ እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት በቤቶች ልማት 32 አማካሪ ድርጅቶች በመሳተፍ ላይ ናቸው፡፡ በዚህ የሥራ ተቋራጮችንና አማካሪዎችን ቁጥር በማሳደግ ሥራ የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች እጥረት ችግር በከፍተኛ ደረጃ ለማሻሻል ተችሏል፡፡ በቀጣይም ይህን ጅምር ዳር በማድረስ የተቋራጮቹንና አማካሪዎችን አቅም ወደ ላቀ ደረጃ ለማሳደግ ተከታታይ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

## II. በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ልማት ፕሮግራም

በፕሮግራም ዘመኑ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በማስፋፋት 1.5 ሚሊዮን ለሚሆኑ የከተማ ሥራ አጥ ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ የነበረ ሲሆን እስከ 2002 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ 1.3 ሚሊዮን ያህል የስራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ ይህን አፈጻጸም ለማረጋገጥ በፕሮግራም ዘመኑ በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የተለያዩ ድጋፎች ተደርገዋል፡፡ ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል 346 ሼዶች ተገንብተው ጥቅም ላይ እንዲውሉና ተጨማሪ 2.87 ሚሊዮን ሜ.ካሬ ስፋት ያለው ቦታ አዘጋጅቶ በማቅረብ የማምረቻና መሸጫ ቦታ ችግራቸውን የማቃለል ሥራ ተሰርቷል፡፡ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ያላቸውን የገንዘብ ችግር ለማቃለል የብር 3.6 ቢሊዮን ብድር ከአበዳሪ ተቋማት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪ ከምርት ሂደት በኋላ የሚያጋጥማቸውን የገበያ ችግር ከመቅረፍ አኳያ ለ220,543 ኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር ተፈጥሮላቸዋል፡፡ እንደዚሁም የንግድ ስራ አመራር እና የቴክኒክና ሙያ ክህሎታቸውን በማሳደግ በገበያው ውስጥ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማስቻል በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በድምሩ 830 ሺህ ለሚሆኑ አንቀሳቃሾች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት አንቀሳቃሾች ቀልጣፋ፣ ውጤታማና የተቀናጀ አገልግሎት የሚሰጡ የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች ማቋቋምና በሰው ኃይል ሚሟላት እንዲሁም የኤክስቴንሽን ኤጀንቶችን የማደራጀት ሥራ በሁሉም ክልሎች ተከናውኗል፡፡ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ልማት ፕሮግራምን ይበልጥ ወጤታማ ለማደረግ የተለያዩ ማስፈጸሚያ ማንዋሎችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው በየክልሉ እንዲዳረሱ በማድረግ አገልግሎቱን የማሳለጥ ሥራ ተሰርቷል፡፡

ከላይ የተገለጹት ድጋፎች የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ልማትን በማጎልበት ረገድ የጎላ አስተዋጽኦ ያላቸው ቢሆንም የተፈጠሩት የሥራ ዕድሎችና ኢንተርፕራይዞች የምርታማነትና የተወዳዳሪነት ችግር የሚታይባቸው መሆኑ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ የተሻለ ጥራት ያለው የኢንዱስትሪ የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት የታዩትን የምርታማነት እጥረቶች ለመቅረፍ መንቀሳቀስ ይጠይቃል፡፡

## III. የከተሞች መሠረተ-ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም

ይህ ፕሮግራም የከተሞችን መሠረተ-ልማትና አገልግሎት በማሻሻል የከተሞች የልማት ማዕከል እንዲሆኑ ለማስቻል አቅማቸውን የሚያጠናክር ፕሮግራም ነው፡፡ በዚሁ መሠረት በልማት ዕቅድ ዘመኑ በዓለም ባንክ በመታገዝ ያልተማከለ አገልግሎት አሰጣጥ አቅም ግንባታ ፕሮጀክት (CBDSD) በ18 ከተሞች ሲካሄድ የቆየ ሲሆን በ142.1 ሚሊዮን ብር በ17 ከተሞች 17 የሚደርሱ የገበያ ማዕከላት፣ የተፋሰስና የጐርፍ ማስወገጃ እና የመንገድ ጥገና ፕሮጀክቶች ሥራ ተጠናቋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የከተሞቹን አቅም ለማሻሻል እንዲረዳ የተለያዩ መሣሪያዎች ተገዝተው ተከፋፍለዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በጀርመን መንግሥት ድጋፍም በ11 ከተሞች 26 የሚደርሱ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ሆነው እስከ 2002 በጀት ዓመት መጨረሻ ይጠናቀቃሉ፡፡

ከእነዚህ ፕሮጀክቶች ትግበራ ጐን ለጐን የከተሞች የመሠረተ ልማት ችግር እና የመልካም አስተዳደር ጉድለቶችን ትርጉም ባለው መልኩ የሚያቃልል የከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት (ULGDP) ተቀርጾ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ፕሮጀክት ከዓለም ባንክ በተገኘ 150 ሚሊዮን ዶላር እና ተጠቃሚ ክልሎችና ከተሞች ደግሞ እያንዳንዳቸው በሚያዋጡት ተጨማሪ 20 በመቶ ገንዘብ በድምሩ 208 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (ብር 2.7 ቢሊዮን ያህል) በ19 ከተሞች የሚካሄድ የመሠረተ-ልማት ፕሮጀክት ነው፡፡ በዚህ ፕሮጀክት እስከ 2002 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ የተለያዩ የመሠረተ-ልማት ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በዚህ ፕሮጀክት ቅድሚያ ከተሰጣቸው ሥራዎች መካከል ዋንኛው የድንጋይ ንጣፍ (Cobblestone) መንገድ ሲሆን እስከአሁንም ከ65 ሺህ ኪ.ሜ በላይ የድንጋይ ንጣፍ ተከናውኗል፡፡ በዚህ ሥራ ብቻ በከተሞቹ ከ46 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ነዋሪዎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በፕሮጀክቱ አማካኝነት ሌሎች የመሰረተ ልማት ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በተጓዳኝም ከጀርመን መንግስት በተገኘ የ15 ሚሊዮን ዩሮ (ብር 195 ያህል) ለተመሳሳይ ሥራዎች በስምንት ከተሞች ለማስፈፀም ቅድመ -ዝግጅቱ በመጠናቀቅ ላይ ነው፡፡

## IV. የከተሞች የመልካም አስተዳደር ፕሮግራም

ፕሮግራሙ በከተሞች ያለውን የመልካም አስተዳደር ሁኔታ በማሻሻል በከተሞች ፈጣን፣ ፍትሃዊና ዘላቂ ልማት ማረጋገጥ፣ እንዲሁም በከተሞች የተሻለ የአስተዳደር ሁኔታ የማስፈንና የከተማ ነዋሪዎች የስልጣን ባለቤትነት የማረጋገጥን ዓላማዎች ይዞ የተቀረጸ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት በ68 የክልል ከተሞች የመሬት አቅርቦቱ በሊዝ ስሪት እንዲተዳደርና

በተጨማሪ በከተሞቹ የሊዝ ጨረታ አሰራር እንዲፈጠር ተደርጓል፡፡ በአዲስ አበባ የመሬትና መሬት ነክ-ንብረት ምዝገባ ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችሉ ዝግጅቶች የተከናወኑ ሲሆን ሌሎች ከተሞች ደግሞ ለዚሁ ለካዳስተር ሥራ ራሳቸውን አደራጅተዋል፡፡ በአጠቃላይ ግን ከእስከአሁን አካሄድ በተለይ በመሬት አስተዳደር ዙሪያ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል እና ወጥነትን የሚያሰፍን ስልት መንደፍና መተግበር እንደሚያስፈልግ በመንግስት በመታመኑ በመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ፣ በመሬት ልማትና አቅርቦት እንደዚሁም በከተማ ፕላን አቅም ግንባታ ላይ ያተኮረ ዝርዝር የማሻሻያ ዕቅድ ተዘጋጅቶና በመንግስት ፀድቆ ተግባራዊ መሆን ጀምሯል፡፡ ከተሞች የጐለበተ የፋይናንስ አቅም እና የተሻሻለ የፋይናንስ የአስተዳደር ሥርዓት እንዲኖራቸው ለማድረግ የተሻሻለ አንድ ወጥና የተጠቃለለ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት በከተሞች ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

በተቋማት አቅም ግንባታ ረገድ የከተማ አስተዳደሮች ማቋቋሚያ አዋጆች በማውጣት ከተሞቻቸው በሕግ እንዲቋቋሙና ተገቢው ነፃነትና የሕግ ድጋፍ እንዲኖራቸው በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ በከተሞች የአገልግሎት አሰጣጥን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ በተለይ በ2001 ዓ.ም. የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት በአብዛኛዎቹ ክልሎች ተጠናቅቆ አዲስ አበባን ጨምሮ በከተሞች ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በቀጣይ የከተሞች ሁለንተናዊ የማስፈጸም አቅምን ለማሻሻል የአሰራር ሂደት ለውጡን በየጊዜው እየፈተሹና እያሻሻሉ ዳር ማድረስ ወሳኝ ይሆናል፡፡

የከተሞች አደረጃጀትና የሰው ኃይል ለማጠናከር ከተከናወኑት ዋና ዋና ተግባራት መካካል የሚጠቀሰው ሌላው ጉልህ ተግባር በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በከተማ ሥራ አመራር የድህረ ምረቃ ዲግሪ ፕሮግራም እስከ ነሐሴ 2001 ዓ.ም. ድረስ በሁለት ዙሮች 1,053 ሰልጣኞች (በማስተርስ ዲግሪ) ተመርቀው ወደ ሥራ መሰማራታቸው ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ደግሞ አንድ ሺህ የሚሆኑ ሰልጣኞች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ናቸው፡፡ ከዚህም

በተጨማሪ ከተሞች እርስ በእርስ እየተማማሩና እየተባበሩ ለመስራት የሚያስችላቸው የትብብር መድረክ በ19 ከተሞች መስራችነት በያዝነው የበጀት ዓመት የተመሠረተ ሲሆን የመጀመሪያ የኢትዮጵያ ከተሞች ቀንም ጥቅምት 13/2002 ዓ.ም. በተለያዩ ዝግጅቶች ተከብሯል፡፡

## V. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አቅም ግንባታ ፕሮግራም

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የሬጉላቶሪ ሥራዎችን በተመለከተ የህንፃ አዋጅና ኢንዱስትሪው የሚመራበትን ፖሊሲ ለማጸደቅ እና ወደ ትግበራ ለማሸጋገር እንቅስቃሴ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በኢንዱስትሪው የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማጎልበት የተለያዩ ሥራዎች የተሰሩ ሲሆን በዚሁም የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እየጎለበተ መጥቷል፡፡ በመሆኑም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተመዘገቡ የኮንስትራክሽን እና ዲዛይን ባለሙያዎች ቁጥር በ1999 ዓ.ም. ከነበረበት 18,401 በ2002 ዓ.ም. ወደ 30,000 አድጓል፡፡ ይሁን እንጂ በኢንዱስትሪው የግል ዘርፉ ተሳትፎ በየጊዜው እድገት ያሳየ ቢሆንም በተለይ በሥራ ተቋራጭ ደረጃ አንድ እና ደረጃ ሁለት ብቃት ያላቸው ሥራ ተቋራጮች በሚፈለገው መጠን ያህል ማግኘት አልተቻለም፡፡ በአጠቃላይ በዕቅድ ዘመኑ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ለማጎልበት ምቹ ሁኔታዎች በመፈጠራቸው የግል የሥራ ተቋራጭ ድርጅቶች፣ አማካሪዎች፣ የግንባታ ቁሳቁስ አቅራቢዎችና የኮንስትራክሽን ማሽን አከራዮች በብዛት ወደ ኢንዱስትሪው መግባታቸው ኢንዱስትሪው በአገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ውስጥ ያለው ሚና እንዲጎለብት አድርጎታል፡፡ የመንግሥት እና የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ አጋርነትን ለማጠናከር የሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በሀገራችን የተደራጁት ስድስት የሙያ ማህበራት በጋራ ሊሠሩባቸው በሚያስችሉዋቸው ጉዳዮች የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል፡፡ ይህም ዘርፉ በአገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ውስጥ ያለው ሚና ከፍ እንዲል እንደሚያደርገው እሙን ነው፡፡

## VI. የመንገድ ልማት ፕሮግራም

የኢትዮጵያ መንግስት ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ የመንገድ ልማት ለሌሎች ልማቶች ፈር ቀዳጅና መሠረት በመሆን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ልማቶችን ለማፋጠን የሚኖረው ሚና የጎላ መሆኑን በመገንዘብ አገሪቱ የምትመራባቸው የልማት ዕቅዶችን በተግባር ለመለወጥ ለመንገድ ዘርፍ ልዩ ትኩረት ሰጥቷል፡፡ ይህን መሠረታዊ ሃቅ ከግምት በማስገባት መንግስት የመንገድ አውታሮችን በጥራትም ሆነ በመጠን ለማሻሻል በ5 ዓመቱ

የልማት ፕሮግራም (1998 - 2002 ዓ.ም.) የመንገድ ዘርፍ ልማት ለማፋጠን በከፍተኛ ቁርጠኝነት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ በርካታ የፊዚካል፣ የፖሊሲ እና የአቅም ግንባታ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ ፕሮግራሙ የበርካታ የልማት አጋሮችን ድጋፍ ያገኘ ሲሆን፣ መንግስትም ከራሱ ለዘርፉ ከፍተኛ በጀት በመመደብ ላይ ይገኛል፡፡ መንግሥት በዚህ በተነደፈው ፕሮግራም አማካኝነት መጠነ ሰፊ የመንገድ ማስፋፋት ሥራ አከናውኗል፣ እያከናወነም ነው፡፡

በመርሃ ግብሩ መሠረት በአምስት አመታት ጊዜ ውስጥ የ904 ኪ.ሜ. የመንገዶች ማጠናከር፣ የ3556 ኪ.ሜ. የዋናና የአገናኝ መንገዶች ማሻሻል እና 2249 የአዲስ መንገዶች ግንባታ ሥራ የተካሄደ ሲሆን 4177 ኪ.ሜ. ከባድ የመንገድ ጥገና ሥራ ተሰርቷል፡፡ ይሄም ታቅዶ ከነበረው 11320 ኪ.ሜ. 10886 ኪ.ሜ. በማከናወን አፈፃፀሙ 96 % ሆኗል፡፡ በዚሁ መርሀ - ግብር ወቅት ወደ አርባ የሚጠጉ የመንገድ ፕሮጀክቶች ሥራቸው ሙሉ ለሙሉ ተጠናቋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በመንገዶች ማጠናከር፣ ማሻሻል እና አዳዲስ መንገዶቸ ግንባታ ርዝመታቸው ከ7000 ኪ.ሜ. በላይ የሚሆኑ የመንገድ ሥራዎች በመከናወን ላይ ሲሆኑ እነዚህም በሚቀጥሉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ውስጥ ሙሉ በሙሉ የሚጠናቀቁ ናቸው፡፡

በዚህም መሠረት የ1998-2002 ዓ.ም. የአምስት ዓመቱ መርሃ-ግብር ሲጀመር የነበረው የፌዴራል መንገድ አውታር 4972 ኪ.ሜ. የአስፋልት መንገድ እና 13640 የጠጠር መንገድ በአጠቃላይ 18612 ኪ.ሜ. ርዝመት ሲሆን፣ በአሁን ወቅት በፕሮግራም ዘመኑ ያለው የፌዴራል መንገድ አውታር ወደ 7262 ኪ.ሜ. አስፋልት መንገድ እና 14900 ኪ.ሜ. ጠጠር መንገድ በአጠቃላይ 22612 ኪ.ሜ. ርዝመት አድጓል፡፡ ይኸውም በአምስት ዓመት ውስጥ 2290 ኪ.ሜ. ያህል አዳዲስ የአስፋልት መንገድ ሥራ እና 1260 ኪ.ሜ. የሚሆን የጠጠር መንገድ ግንባታ መካሄዱን ያሳያል፡፡ ይኸንንም የግንባታ ሥራ ለማከናወን ከመንግስት ካዝና እና ከልማት አጋሮች በተገኘ በአጠቃላይ ብር 38 ቢሊዮን ያክል ወጪ ተደርጓል፡፡

በተጓዳኝም የመንገድ ፈንድ ለመንገድ ጥገና እና ለመንገድ ደህንነት ርምጃዎች ማስፈፀሚያ የሚውል ተከታታይ የፋይናንስ አቅርቦት እንዲኖር በማድረግ የፌዴራል መንገዶች፣ የክልል ገጠር መንገዶች እና የከተማ መንገዶች ተከታታይ ጥገና እንዲያገኙ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ባለፉት አምስት ዓመታት (ከ1998 - 2002) ውስጥ ብር 5.8 ቢልዮን ገቢ በመሰብሰብ በሚቀርቡለት የክፍያ ምስክር ወረቀት መሰረት ለተሰሩ ስራዎች ብር 5.4 ቢልዮን ክፍያ ፈጽሟል፡፡ በዚሁ አምስት ዓመት ውስጥ ከመንገድ ፈንድ በተመደበ በጀት ወቅታዊ መደበኛ የጥገና ሽፋን ያገኘው የመንገድ ርዝመት በሥራ መጠን ሲለካ 110987 ኪ.ሜ ያህል ይሆናል፡፡

(ይህ አሃዝ እስከ ሰኔ 30/2002 የሚኖረውን የፈንዱን ገቢና ወጪ ግምት ያካተተ ነው፡፡)

የእነዚህ የመንገድ ግንባታ ሥራዎች መካሄድ አብዛኛው የአገሪቱ ክፍሎች እርስ በርስ በመንገድ እንዲገናኙ ያደረገ ሲሆን አብዛኛው የግብርናው ሕብረተሰብም የግብርና ውጤቱን ወደ ገበያ ማቅረብ በመቻሉ ኑሮውን ለማሻሻል በቅቷል፡፡ በተጨማሪም የትራንስፖርትን ዋጋ ተመጣጣኝ እንዲሆን እገዛ አድርጓል፡፡

ሲጠቃለል በአምስት ዓመቱ መርሃ-ግብር ወቅት 40 የሚሆኑ ዋና ዋና መንገዶች ሙሉ ለሙሉ ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት የቻሉ ሲሆን፣

1. ከሞላ ጐደል ሁሉም የክልል ዋና ከተሞች ደረጃውን በጠበቀ አስፋልት መንገድ የተገናኙ ሲሆን ጥቂት ኪ.ሜ. የቀራቸውም ቢሆን እስከ ሰኔ 2002 ድረስ ሙሉ በሙሉ በአስፋልት የሚገናኙ ይሆናል፡፡
2. በርካታ የአገናኝ መንገድ ፕሮጀክቶችም በመጠናቀቃቸውና በመካሄድ ላይ ያሉ ስለሆነ በርካታ አካባቢዎች ከመንገድ እጦት እየተላቀቁ ይገኛሉ፡፡ በዚህም በተለይ አርሶአደሩ ምርታማነቱን እንዲጨምርና ሰፊ ገበያ እንዲያገኝ ረድቶታል፡፡ የህዝቡን ወደተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች የሚደረገውን እንቅስቃሴ ከጊዜና ከወጪ አንፃር ቀላልና ምቹ አድርጐለታል፡፡
3. በዚሁ መርሃ-ግብር ወቅት አገራችን በዓይነቱ ልዩ የሆነው የአዲስ አበባ-አዳማ ባለ-ስድስት መስመር (Lane) ሥራ መጀመር የመንገድ ዘርፉ መንገዶችን ለኢኮኖሚው ዕድገት በሚመጥን ዓይነት ወደላቀ ዘመናዊ ደረጃ ማሸጋገር የጀመረበትም ወቅት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡
4. የአገር በቀል ተቋራጮች ተሳትፎ የመንገድ ዘርፍ ልማት መርሃ-ግብር ሲጀመር ከነበረበት ዝቅተኛ ደረጃ (ያልነበረ ማለት ይቻላል) ተነስቶ በ13 ዓመታት ብር 22 ቢሊዮን በሚያወጡ ሥራዎች እንዲሳተፍ ያስቻለ ፕሮግራም ነው፡፡  በየጊዜው በሚደረግለት ድጋፍ ተሳትፎው እያደገ ትርጉም ያለው እንቅስቃሴ ማድረግ የጀመረ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት አገራዊው ተቋራጭ በአማካይ በዓመት 5 ቢሊዮን ብር የሚያወጣ የዋና መንገዶች ኮንትራት መፈራረም ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡

በዘርፉ ያለውን የመንገድ ልማት እንቅስቃሴ በተሻለ መልኩ በቀጣይነት ለማስኬድ እንዲያስችል ቀደም ብለው በአፈፃፀም ላይ የታዩ ችግሮችን መቅረፍ እና ዘለቄታዊ መፍትሔ መስጠት በቀጣዩ የልማት መርሃ-ግብር ከመንገድ ዘርፉ የሚጠበቀውን ውጤት ለማምጣት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በመጪው ጊዜ በአሁኑ ወቅት በመገንባት ላይ ያሉ የመንገድ ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ እና በርካታ አዳዲስ የመንገድ ፕሮጀክቶችን በመገንባት የልማት ዕድገቱን ለማፋጠን የሚያስችል አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር በዘርፉ ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ አካላት በሙሉ የአፈፃፀም ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ ወሳኝ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በአጠቃላይ በቤቶች ልማት፣ በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት፣ በከተሞች መሠረተ-ልማት፣ በከተሞች መልካም አስተዳደር እና በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሬጉላቶሪ ሥራዎች ዙሪያ የተከናወኑ ተግባራት ለተያያዝነው የልማትና የመልካም አስተዳደር ግብ መሳካት ትልቅ ትርጉም ያላቸው ናቸው፡፡ በተለይ ደግሞ በመንገድ ልማት ፕሮግራሙ መንግስት ኢንቨስት ባደረገው ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በሁሉም ክልሎች የሚከናወነው የመንገድ አውታሩ ዝርጋታ ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ እያደረገ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም በቀጣይ የተገኙትን ውጤቶች ይበልጥ በማጎልበትና ሳይፈጸሙ የቀሩትን ደግሞ አሟልቶ በማከናወን አጠቃላይ የፕሮግራሞቹን አፈፃፀም ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ ይገባል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የእስከአሁኑን አፈፃፀም ግምት ውስጥ ያስገባ የቀጣዮቹ አምስት ዓመታት ዕቅድ በማዘጋጀት ላይ ናቸው፡፡ በዚህም ክፍለ-ኢኮኖሚው የላቀ ውጤት ለማረጋገጥ እንደሚችል እምነቱ አለኝ፡፡

**አመሰግናለሁ !!**